## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሐምሌ 3/2001

### የሱዳን ወታደር በኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ላይ ግድያ አካሄደ

ሐሙስ ሐምሌ 1 ቀን የሱዳን ጦር ቲሀ በተባለው የድንበር ከተማ ገፅ ድንገተኛ ወረራና ጥቃት አካሂዶ በእርሻ ስራ የተሰማሩትን በርካታ አርሶ አደሮች መግደሉን ማወቅ ተችሏል፡፡ በአካባቢውየነበረው የወያኔ የታጠቀ ሀይል ሕዝብ ሲጨፈጨፍ እጁን አጣጥፎ መመልከቱም ተዘግቧል፡፡ ጥቃት የደረሰባቸው አርሶ አደሮች 7 አስከሬን ሊያነሱ ችለው አንዱ ዜጋ መተማ ሲቀበር ሌሎቹ ወደነጋዴ ባሕርና የጭልጋ ክፍሎች ተወስደዋል፡፡

በነፍሶ ገበያ ሰፍሮ አርሶ አደሩን ያጠቃውና ያባረረው የሱዳን ጦር በቲሀም ገፅ መሬት የተሰጠው በመሆኑ መሬት ለማስለቀቅ የሀይል እርምጃ የወሰደው የወያኔ አገዛዝ ሙሉ ድጋፍ እንዳለው አረጋግጦ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በቅርቡም ከወያኔ ጋር ወታደራዊ ስምምነት የተፈራረመው ሱዳን ይህ በሕዝብ ላይ የፈፀመውን ግድያ በተመለከተ ዜጎች በተገቢው መንገድ የሚበቀሉ ለመሆናቸው ጥርጥር የሌለው ሲሆን በዚሁ ፀረ ሕዝብና ፀረ ኢትዮጵያ ወንጀል የመለስ ዜናዊ ከሀዲ አገዛዝ ዋና ተጠያቂ ነው፡፡ የሀገራችንን ሉዓላዊነት ያስደፈረው የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ትግላችን መጠናከር አለበት፡፡ በሱዳን እየተጠቃ ላለው ሕዝብም ድጋፋችንን በተገቢው መንገድ ማድረግ አለብን ሲል ኢሕአፓ ጥሪ እነሆ ያስተላልፋል፡፡

ኢትዮጵያን የሚያስደፍረው ፀረ ሕዝብ የወያኔ አገዛዝ በትግላችን ይወገድ!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France